ለርእሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን Mar19/13

አይንቲነ ካህናት አገልጋዮች እና መላው የቤተክርስቲያኑዋ ልጆች ምእመናን

የጠሉት ይወርሳል የፈሩት ይደርሳል ሆነና መሸናነፍ የሌለው ውጤት እኩል ለኩል ነው እኩል ለኩል ደግሞ ውድቅት ሆነ ይሄ ደግሞ የኢትዮጲያ ኦ.ተ.ቤ ልጆችን ሁሉ ያሳዘነና ይሳፈረ ሆነ እኔ ከሁለት አመት በላይ ስከታተለው ሀሳቤን በጽሁፍ ባልገልጽም ከምእመኑም ከካህናቱም ጋር ተነጋግሬበታለሁ ስጋቴንም ለመግለጽ ሞክሪአለሁ መቼም ዘርፈ ብዙ ችገረኞች ሆነን ቸግርና መከራን እንግልትና ስቃይን እየለመድነው መጣን መሰለኝ ግማሾቻችንም ዝምታን መርጠን ተቀመጥን የተቀረነውም ወዲህና ወዲያ እያልን ችግረን አባባሾች ሆነናል ያለመታደል ሆነና የቀረነውም ጉድ ጉድ እንላለን የተቀረውም ይባባሉ ይላል ቀደም ሲል አባቶቻችን ችግር ሲገጥማቸው ከአንዴ ከሁለቴ በላይ አይወያዮበትም ወድያው ውደግዚአብሄር ነው አቤቱታቸው መልስም ያገኙ ነበር የጸሎት ሀይል ይረዱ ነበርና ዛሬ ህዝባችን መከራ ላይ ነው ገዳማቶቻችን እየተቃጠሉ እይታረሱ አባቶች እየተሰደዱ ቤተክርስቲያን ስለነዚህ አደጋዎች ሁሉ የጾም አዋጅ የጸሎት አዋጅ ቀርቶ በመወያየት በመነጋገር ችግር ለመፍታት ሆነ መቼም መነጋገርና መወያየት ባይጠላም መጠን ገደብ የሌለው መነጋገር እና መወያየት በመንፈሳዊ ቤት ውጤት አያመጣም ዋልድባ ገዳም ከመታረሱ በፊት አንድ በግብጽ በረሀ ላይ የሚኖሩ አባት አባ ገበረ መስቀል ዋልድባ የሚታረስበት ዘመን ይመጣል በማለት ከ12 አመት በፊት ይናገሩ ነበር ቤተክርስቲያንም ልጆቹዋም ሰምተው ያን ዘመን በጉጉት ሲጠብቁ ዘመኑ ቀረበና አዩት ደግ ዘመን ሳይሆን ከፉ ዘመን ለማየት የምንጉጉዋ ትውልድ ሆንን የደርግ ዘመን መውደቂያና ወያኔ ወደ አዲስ አበባ ሲገባ ባህታውያን ህዝቡን ያስጠነቅቁ ነበር እሳት ከሰማይ ይወርዳል ጸልዩ እያሉ ህዝብ ሰብሰበው ሲያስተምሩ እሳት ይወርዳል ሲባል እንቁላል ጠብሰን እንበላበታለን የሚል ጥፋት እስኪደርስበት የማያምን ትውልድ ተፈጠረ በርምጃችንም በስራችንም ደርሰን ካላየነው የውደፊት ወጤታችንንም ማውቀ ባለመቻላችን ሆልጌዜ መውደቅ ሆነ እስቲ ከውድቀትም ብንማር ጥሩ ነው የሁለት አመት የስብሰባ ውጤት አራት ኪሎ የተቀመጠውን ሰይጣን ስንፈራ እርሱ የደም ግብር የሚያቀርብላቸውን መናፍስት ሳንረዳ ቀርተን ዛሬ እዚህ ላይ ደረስን **መጽሀፈ ነገስት ቀዳማዊ ም9 ቁ7 ትእዛዜን እና ሰራቴን ባትጠብቁ ከሰጠሁአችሁ ምድር አጠፋችሁዋልሁ ለስሜም የቀደስኩትን ይህንን ቤት ከፊቴ እጥለዋለሁ በአህዛብም ሁሉ መካከል ምሳሌና ተረት ትሆናላችሁ** እያለ እስራኤላውያንን ወቀሰ እኛም አሁን ዛሬ በዚህ 20 አመት ከሰሜን በመጡ አጥፊዎች እለት እለት ሀገር እያጣን ሀብት እያጣን በአህዛቦች ሁሉ ፊት ተረትና ምሳሌ ሆንን. **አቤቱ እኛ ደክመናልና ስለኛ ብለህ ሳይሆን ስለነዛ ደጋግ አባቶቻችን ብለህ አንተ በመሀከላችን ግባ።**

አሁንም በመሃከል የገባውን እርኩስ መንፈስ ለማስወገድ የእልህ ጉዞ የምትጉዋዙ ሆሉ ቆም ብላችሁ አብራችሁ ተባብራችሁ ይህን ህንጻ የገዛችሁበትን ያን እረዥም የፍቀር አመታት ተመልከቱ የዛሪውን ሳይሆን የትናንቱን መቀራረብ አይታችሁ ለመራራቅ ሳይሆን ለመቀራረብ መፍጠን ተገቢ ነው ለዝች ቤተክርስቲያን ማንም ባለቤት ማንም ባይተዋር የለም አገልጋዮችም ምእመኑም ባለቤት ነው ሁሉም ዋጋ ከፍሎአል የኢትዮጲያ ቤተክርስቲያን ሙስሊሙም ጁሹም ኢትዮጲያዊው ሁሉ ባለቤት ነው የሚበጀው አንዳችሁ ለአንዳችሁ ዝቅ ማለት ትልቅነት ነው መቼም ግዢዎቻችን መልካም ባህላችንን አጥፍተው መጥፎ ባህል አላምደውን ጠቡ ሌላ ክሱ ሌላ ስም መጠፋፋቱም ቤተክርስቲያንን ሀገርን ይጎዳል ትውልድም ያጠፋል ስለዚህ እግዚአብሄርና ሰው የሚገናኙበት በአመት አንዴ በጉጉት የሚጠበቅ ትልቅ ጾም በመሆኑ እስከወዲያኛው እንዳይሔድ በመጀመሪያ እረቀ ሰላም ይውረድ በመቀጠልም በሁለታችሁም መካከል ያልነበረ ሁለታችሁም የምትመርጡት ነገሩን በጥሞና ሊያስረዳ የሚችል ሰዎች እንድያነጋግሩዋችሁ ማመቻቸት ቤተክርትያኑዋ ተከፍታ ስራዋን እንደቀድሞ ታካሂድ ዘንድ ሁለታችሁም ስትነጋገሩ የቆያችሁ በግዚአብሄር ስም በፍቅር የምትነጋገሩበትን መንገድ አመቻቹ ለዚህም የቤቱ ባለቤት ቀድስት ድንግል ማሪያም ትርዳችሁ

እግዚአብሄር አምላካችን ሆይ በደላችን በዝቱአልና እባክህ ይቅርታህን አውርድልን
የአንድ ቤተሰብ ልጆች ተለያይተን ሁለት አስርት አመታት ሆነን እረግጠው የያዙንን
የጥፋት ሀይሎች አስወግደህ በፍቅር በመተሳሰብ የምንኖርባትን ምድር መልስልን

ወንድወሰን
Coventry 2o13 Mar19